አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፪ ፪ሺ፭ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

FIFTH YEAR NO.54
ADDIS ABABA OCTOBER 1/2012

**ማውጫ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ደንብ.............................ገፅ ፮፻፵፪

## ደንብ ቁጥር ፶፬/ ፪ሺ፭

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ጥሰትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ መተላለፍና ሌሎች ሕገወጥ ተግባራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ በመምጣታቸው፤

በከተማው ውስጥ የደንብ መተላለፍና ተያያዥ ሕገወጥ ተግባራትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም አግባብነት ያለውን እርምጃ ለመውሰድ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት በአዋጅ ቁጥር ፴፯/፪ሺ፭ የተቋቋመ በመሆኑ፤

የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት አደረጃጀት እና አሠራርን በዝርዝር የህግ ማዕቀፍ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ያንዱ ዋጋ
Unit price

**CONTENTS**

THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT CODE ENFORCEMENT SERVIES REGUL ATION……...........................PAGE 642

## Regulation No.54/2012

## A Regulation to Provide for the Prevention and Control of Code Violation and Organizational Structure and Working Procedure of Office of Code Enforcement of Addis Ababa City Government

**WHEREAS**, Code violations and other illegal activities are increasing from time to time in the Addis Ababa City Government;

**WHEREAS,** the Code Enforcement Service Office has been established by Proclamation No 37/2013 to prevent, control and take appropriate measures on code violations and other illegal activities;

**WHEREAS,** it has been found necessary to provide organization al structure and workprocedure for the Office of Code Enforcement Service by detail legal framework;

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ በአንቀጽ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ደንብ ቁጥር ፶፬/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ከንቲባ"** ማለት የከተማውን አስተዳደር የሚመራ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው፤

፬. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፯ /፪ሺ፭ ነው፤

፭. **"የቁጥጥር ኦፊሰር"** ማለት በዚህ ደንብ የተመለከተውን የደንብ መጣስ ተግባር ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተቀጠረ ወይም የተመደበ የደንብ መተላለፍ ክትትልና ቁጥጥር ኦፊሰር ነው፤

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 23(1) (f) of the Revised Charter of Addis Ababa City Government Proclamation No 361/2003 and Article 84 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No 35/2004 the City Cabinet has issued this Regulation as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government Code Enforcement Service Regulation No. 54/2012".

### 2. Definitions

Unless the contest otherwise requires, in this Regulation:

1. **"City"** means the Addis Ababa City;
2. **"Government"** means the Addis Ababa City Government;
3. **"Mayor"** means the chief executive officer of the City Government;
4. **"Proclamation"** means the Proclamation to Re-amend Proclamation No. 35/2012 of the Addis Ababa City Government Executive and Municipal Service Organs Re-establishment Proclamation No. 37/2013;
5. **"Control officer"** means an officer of code violation follow up and control who is employed or assigned to control and prevent act of code violations stipulated by this Regulation;

፮. **“ሕገወጥ የመሬት ወረራ”** ማለት አግባብ ካለው የከተማው አስተዳደር አካል ፈቃድ ሳይገኝ መሬትን መያዝ ነው፤

፯. **“ሕገወጥ የመሬት ይዞታ ማስፋፋት”** ማለት አግባብ ካለው የከተማው አስተዳደር አካል በሕጋዊ መንገድ ከተሰጠው ቦታ በተጨማሪነት አስፋፍቶ መያዝ ነው፤

፰. **“ሕገወጥ ግንባታ”** ማለት በሕገወጥ የመሬት ወረራ ወይም በሕገወጥ የመሬት ይዞታ ማስፋፋት በተያዘ ቦታ ወይም በሕጋዊ ይዞታ ላይ ያለግንባታ ፈቃድ የተገነባ ማንኛውም ግንባታ ነው፤

፱. **“ሕገወጥ የመንገድ ላይ ንግድ”** ማለት በከተማ አስተዳደሩ በተወሰኑ ቀናት በመንገድ ላይ ለመነገድ ከተፈቀደባቸው መንገዶች ወይም ከንግድ መደብሮች በስተቀር በሌላ ማንኛውም መንገድ ወይም ቦታ የሚካሄድ ንግድ ነው፤

፲. **“መንገድ”** ማለት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ዋና መንገዶች፣ መለስተኛ መንገዶች፣ መጋቢ መንገዶች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የመንደር መንገዶች፣ አደባባይ እና የአደባባይ ዙሪያዎች፣ የመንገድ አካፋይ ደሴቶች፣ በመንገድ ግራና ቀኝ ያሉ የእግረኛና የቢስክሌት ማስተላለፊያዎች፣ ድልድይ እና የጎርፍ ማስወገጃ መስመሮችን እና በከተማው መሪ ፕላን መሠረት ለመንገድነት የተያዘን ቦታ ይጨምራል፤

፲፩. **“ደረቅ ቆሻሻ”** ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከተቋማት፣ ከጋራዥ፣ ከመንገድ ፅዳት፣ ከግንባታ፣ ከግብርና፣ ከመሬት ቁፋሮና በጠቅላላው ከሕብረተሰቡ ሥራዎችና በእንስሳት ምክንያት የሚፈጠር፣ ጠጣርና ከፊል ጠጣር ቆሻሻ ነው፤

6. **“Illegal land invasion”** means occupying land without securing permission from the appropriate organ of the City Government;

7. **“Illegal expansion of possession”** means expanding land into possession in addition to legally entitled plot by the appropriate organ of the City Government;

8. **“Illegal construction”** means any construction undertaken; on a land which is possessed illegally, on a land expanded illegally, or on a legal possession without securing permission;

9. **“Illegal street vendering”** means a trading activity undertaken on any street or place except the street or business permited by the City Government for limited days ;

10. **“Road”** means main roads, cross roads, arterial roads and sub-arterial roads, squares, road midians, right and left side of pedestrian and bicycle passages, bridges and flooding drainage lines found in the City Governmet and plots of land reserved for road by the master plan of the City;

11. **“Solid waste”** means solid and semi solid waste generated from house holds, business, industries, institutions, street sweeping, construction, agriculture, land quarry and generally wastes generated from activities of the society and animals;

፲፪. **“ፈሳሽ ቆሻሻ”** ማለት ከመኖሪያ ቤትም ሆነ ከማንኛውም ድርጅት የሚወጣ የልብስ፣ የምግብና መጠጥ ዕቃዎች እጣቢ፣ አተላ፣ አምቡላ፣ የመፀዳጃ ቤት ፈሳሽ፣ የእንስሳት ማደሪያ ፍሳሽ፣ መርዛማ ንጥረ ነገር ያዘለ ወይም ያላዘለ ፍሳሽ ነው፤

፲፫. **“ጽህፈት ቤት”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህ ፈት ቤት ነው፤

፲፬. **“የሥራ ሂደት”** ማለት የጽህፈት ቤቱን ተግባር እንደየአግባቡ ለመፈፀም ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ የተደራጀ የሥራ ክፍል ነው፤

፲፭. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚፈ ጸም የደንብ መተላለፍ እና ተያያዥ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**፬. <u>የፆታ አገላለጽ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተ ቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት፣ ተጠሪነት፣ሥልጣንና ተግባር

**፭. <u>አደረጃጀት</u>**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. ዋናና ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣

፪. አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች፣

፫. አስፈላጊ ሠራተኞች ፣

፬. በክፍለ ከተማና ወረዳ በጽህፈት ቤት ደረጃ ተደራጅቶ የተለያዩ የስራ ክፍሎች እና አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡



12. **“Liquid waste”** means liquid waste incorporating toxic or non-toxic substances that are released from households or any organization such as laundry, sanitary, beverage, latrine, sewerage and animal wastes;
13. **“Office”** means the Addis Ababa City Government Code Enforcement Service Office;
14. **“Business process”** means a work unit organized to implement the function of the Office from the City level to Wereda level;
15. **“Person”** means natural or legal person.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall be applicable on code violations and other related illegal activities commited within the City Government.

**4. <u>Gender Reference</u>**

Unless otherwise expressed, in this Regulation expressions stated in the masculine gender shall apply to the feminine gender.

## PART TWO
## STRUCTURE, ACCOUNTABILITY, POWER AND FUNCTION

**5. <u>Structure</u>**

The Office shall have the following structure:

1. General manager and Deputy manager,
2. Necessary departments,
3. Necessary staff,
4. At the Sub-City and Wereda level it shall be organized at Office status and have different work units and necessary staff.

**፮. ተጠሪነት**

፩. ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለከተማው ከንቲባ ነው፤

፪. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተደራጀው ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈጻሚ እና ለከተማው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ይሆናል፤

፫. በወረዳ ደረጃ የተደራጀው ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ እና ለክፍለ ከተማው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

**፯. የጽህፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ጽህፈት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር ፴፯/፪ሺ፭ የተሠጠው አጠቃላይ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክፍለ ከተማና የወረዳ ጽህፈት ቤቶችን በማስተባበር የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በከተማው አስተዳደር ክልል የሚፈፀም የጽዳት መጓደል፣ ሕገወጥ የመንገድ ላይ ንግድ ፣ ሕገወጥ ግንባታ፣ ሕገወጥ የመሬት ወረራ፣ ሕገወጥ የመሬት ይዞታን ማስፋፋት፣ በሕገወጥ መንገድ የውጭ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ መትከል፣ ማንጠልጠልን ይከላከላል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፪. በክፍት እና ዝግ የመናፈሻ ቦታዎች፣ የመንገድ አካፋዬች፣ ዳርቻዎችና አደባባዬች የሚከናወኑ ሕገወጥ ተግባራትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል እርምጃ ይወስዳል፤

፫. ሕገወጥ ዕርድን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

፬. ባልተፈቀደ ቦታ የእንስሳት ዝውውር እና ግብይትን ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

**6. Accountability**

1. The Office shall be accountable to the Mayor of the City;
2. The accountability of the Code Enforcement Office organaized at Sub-City level shall be to the Sub-City Chief-Executive and to the City's Code Enforcement Office;
3. The accountability of the Code Enforcement Office organaized at Wereda level shall be to the Werda Chief-Executive and to the Sub-City Code Enforcement Office.

**7. Power and Function of the Office**

Notwithstanding, the power and function vested to it by Proclamation No 37/2013 and other laws, by coordinating the Offices at Sub-City and Wereda level, the Office shall have the following detail powers and functions:

1. Prevent, control and take legal measure on insanitary actions, illegal street vendering, illegal construction, illegal invasion of land, illegal expansion of land possession, affixing, erecting and hanging illegal outdoor advertisement within the City Government;

2. Prevent, control and take measure on illicit activities undertaken on open and close park areas, road cordon, sidewalks, and squares;

3. Prevent, control and take measure or cause measure to be taken on illegal slaughtering;
4. Control and take measure on animals trading and traficking at prohibited places;

፭. ሕገወጥ የፈሳሽ እና የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽን ከጎርፍ ማስወገጃ መስመር ጋር ማገናኘትና መልቀቅ፣ የማንሆሎችን ክዳን መክፈት፣ ፉካዎችን እና የጎርፍ ማስወገጃ መስመርን መድፈን ወይም ጉዳት ማድረስን ይከላከላል፣ይቆጣጠራል እርምጃ ይወስዳል፤

፮. ያለ ፈቃድ አሸዋ፣ አፈር፣ ማንኛውንም ተረፈ ምርቶችን በመንገድ ላይ መድፋት ማንጠባጠብ፣ ድንጋይ ወይም እንጨት መፍለጥን፣ አጣና በማውረድ መከመርን ጭቃ ማቡካትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፯. በመንገድ ላይ የተበላሸን ተሽከርካሪ ማቆም፣ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ መጠገን ወይም ማስጠገን፣ ማጠብ ወይም ማሳጠብን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፰. መንገዶችን ማሻሻል፣ መቀየር፣ መቀየስ፣ በበር መዝጋት፣ በኬላ ማጠር መቁረጥን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፱. በመንገድ ላይ የንግድ ዕቃዎችን ለረዥም ጊዜ ማስቀመጥ፣ ዛፍ ወይም አትክልት መትከል፣ ያለፈቃድ ድንኳን መጣል፣ የብየዳም ሆነ ሌላ ማንኛውንም የትራፊክ እንቅስቃሴንና ዕይታን የሚከላከሉ ተግባራትን ይቆጣጠራል፣ ይከላከላል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፲. በድልድዮች፣ በመንገድ መብራቶች፣ በትራፊክ መብራቶች፣ በእግረኛ መከላከያዎች ምልክትን ማጣመም ወይም ማበላሸትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

5. Prevent, control and take measure on illegal linking and releasing of liquid and toilet sewerage with flood drainage lines, opening manhole covers, causing damage or filling up of flood drainage and fukas;

6. Prevent, control and take measure on deploying sand, soil and any by-product, logging of stones or woods, dropping and putting of trees and mixing soil on roads without securing permission;

7. Prevent,control and take measure on parking defective vehicle, repairing or cause vehicle to be repaired , washing or cause vehicle to be washed on the roads;

8. Supervise, control and take measure on upgrading, changing, surveying, closing, barricading and cutting roads ;

9. Prevent,control and take measure on putting commercial items for long period of time, planting tress or plants, building tent without permeation, welding or any other activities that mass the traffic activity and view on roads ;

10. Prevent, control and take measure on breaking and damages on bridges, road lights, traffic lights and pedestrian barriers;

፲፩. በመንገድ መብራት ምሰሶ፣ በድልድይ፣ በመንገድ ምልክት እና በእግረኛ የመንገድ መከላከያ አጥር ላይ ባነር፣ ማስታወቂያ ወይም የማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ ወይም መት ከልን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፪. የትራፊክ እንቅስቃሴ እና ደህንነትን የሚያውኩ በመንገድ ወይም በትራፊክ መብራት ላይ የሚከናወን ልመናን፣ንግድን ወይም ሌላ ማንኛውም የትራፊክ እንቅስቃሴን የሚያውክ ወይም ለአደጋ የሚያጋልጥ ተግባርን ከትራፊክ ፖሊስ ጽህፈት ቤት ጋር በቅንጅት ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣እርምጃ ይወስዳል፤

፲፫. በማናቸውም የመንግስት ሀብትና ንብረት ላይ ስርቆት እንዳይፈፀም ይከላከላል፤ ስርቆት ተፈጽሞ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አግባብ ላለው አካል ያሳውቃል፤

፲፬. ጫት ማስቃምን ወይም ሺሻ ማስጨስን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፭. በትምህርት ተቋማት ዙሪያ ዕፅ መጠቀሚያ ቤት፣ ፊልም ወይም ቪዲዮ ቤት፣ ጭፈራ ቤት፣ መጠጥ ቤት፣ ቁማር ቤት መክፈትን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፮. በከተማው አስተዳደር ከደንብ ማስከበር ጋር በተያያዘ የወጡ ደንቦችን፣ ስለሚደረጉ ቁጥጥሮች እና ስለሚወሰዱ ዕርምጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ያስጨብጣል፤

፲፯. ከጽህፈት ቤቱ ተልዕኮ አንፃር በደንብ መጣስ ተግባሮች ላይ ቅድመ ጥናት ያደርጋል፣ በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ይፈፅማል፤

11. Prevent, control and take measure on affixing or erecting banner, advertisement or advertisement board on light pol, bridge, road sign and pedestrian barrier;

12. Prevent, control and take measure in collaboration with the office of traffic police on begging activities, commercial or any other activity practiced on traffic light or road which makes the the traffic flow disturbed or vulnerable to accident;

13. Prevent theft on public property; when it happened shall inform to the relevant organ to take appropriate legal measure;

14. Prevent, control and cause measure to be taken, in collaboration with concerned organ, on the chewing of chat or smoking of shisha;

15. Prevent, control and take measures in collaboration with concerned organ on the opening of drug usage houses, film or video houses, night clubs, grocery and gambling houses around school compounds;

16. Create awareness to the society by using different methods on issued regulations related to code enforcement, performed supervisions and measures taken;

17. Undertake prior research on code violations with regard to the mission of the office and take action inline with the outcome the research ;

፲፰. በገንዘብ የሚያስቀጡ የደንብ መጣስ ተግባራትን የቅጣት ገቢ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ሕግ መሠረት እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤

፲፱. ከደንብ ጥሰትና ማስከበር ጋር በተያያዘ ከከተማው አስተዳደርና ሌሎች መስሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅትና በትስስር ይሰራል፤

፳. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቁጥጥር ኦፊሰርን ከአንድ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ ወደ ሌላ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት በመመደብ ሊያሰራ ይችላል፤

፳፩. የቁጥጥር ኦፊሰሮች የስነ-ምግባር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋ፡፡

## ፰. የጽህፈት ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

የጽህፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ፡-

፩. ጽህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፪. የጽህፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፤

፫. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬. ለጽህፈት ቤቱ በተመደበ በጀትና የሥራ ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፭. ከሶስተኛ ወገን ጋር ለሚኖረው ግንኙነት ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፤

፮. የጽህፈት ቤቱን ሰራተኞች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፤

፯. ስለ ጽህፈት ቤቱ የሥራ አፈፃፀም ወቅታዊ ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፤

፰. በከንቲባው ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

18. Cause the collection of revenue generated from fine resulted from petty offence in accordance with the City Government's finance law;
19. Work in coordination and cooperation on matters related to code violation and enforcement with other City Government Offices;
20. Permanently or temporarily deploy control officers from one Sub-City or Wereda to another Sub-City or Wereda , if necessary;
21. Issue and implement code of ethics for control officers.

## 8. Power and Function of the Manager of the Office

The General Manager of the Office shall:

1. direct and coordinate the Office;
2. implement the powers and functions of the Office;
3. prepare the annual plan and budget of the office, and implement the same upon approval;
4. effect expenditure in accordance with allocated budget and plan of the Office; and supervise appropriate implementation of the same;
5. represent the Office in its relationships with third parties;
6. recruit and dismiss employees of the Office in accordance with the relevant law;
7. submit timely performance report of the Office to the Mayor;
8. perform such other activities specifically entrusted to him by the Mayor.

፱. <u>**የጽህፈት ቤቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**</u>

፩. ዋና ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

፪. በዋና ሥራ አስኪያጁ ወይም በከንቲባው ተለይተው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ስለ ቁጥጥር ኦፊሰሮች</u>

፲. <u>**የቁጥጥር ኦፊሰሮች ምልመላና ሥልጠና**</u>

፩. የቁጥጥር ኦፊሰሮች ሥነ ምግባራቸውና የአካል ብቃታቸው እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው መስፈርቶችን በማሟላት በወረዳው ነዋሪ ተወካዮች ሲመሰከር ይመለመላሉ፤

፪. የቁጥጥር ኦፊሰሮችን ምልመላ ለማስፈፀም በየወረዳው አግባብነት ካላቸው አካላት የተውጣጣ ኮሚቴ ይቋቋማል፤

፫. በኮሚቴው የተመለመሉ ዕጩዎች ወደ ሥልጠና ከመግባታቸው በፊት ኅብረተሰቡ አስተያየት እንዲሰጥ ለህዝቡ ግልጽ በሆነ ቦታ ዝርዝራቸው ይለጥፋል፤

፬. የተመለመሉ የቁጥጥር ኦፊሰሮች አግባብነት ያለውን ሥልጠና መውሰድና ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ለሥራው ይቀጠራሉ፤

፭. የቁጥጥር ኦፊሰሮች ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በከተማው አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፤

፮. የተመለመለ ዕጩ የቁጥጥር ኦፊሰር በሥልጠና ሂደት ብቁ ያለመሆኑ ከተረጋገጠ የመቀጠር መብት አይኖረውም፤

፯. ማንኛውም በቁጥጥር ኦፊሰርነት የተቀጠረ ሰው የ፫ አመት የአገልግሎት ግዴታ አለበት፤

9. <u>**Power and function of the Deputy Manager of the Office**</u>

1. Shall act on behalf of the General Manager in case of absence or incapacitation of the latter ;
2. Shall discharge other duties which may be specifically entrusted to him by the General Manager or the Mayor.

## <u>PART THREE</u>
## <u>CONTROL OFFICERS</u>

10. <u>**Recruitment and Training of Control Officers**</u>

1. Control officers shall be recruited after they are witnessed by the representatives of the dwellers of every Wereda by fulfilling ethical, physical fitness and other relevant criterias;
2. A committee shall be established from the relevant organs of the wereda to implement the recruitment of the control officers;
3. The list of the recruited candidates by the committee shall be posted on public place before they enter into training;
4. The recruited candidates shall be employed only when it is insured that they have taken the relevant training and competent;
5. Salary and other incentives of the control officers shall be determined by the Civil Service Agency of the City Government;
6. The recruited candidate for control officer has no right to employment if he is found unfit during the training;
7. Any person employed as a control officer shall serve for a compelsory period of 3 years;

፰. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፯) የተቀመጠውን የአገልግሎት ጊዜ ሳያጠናቅቅ ከስራው የሚለቅ የቁጥጥር ኦፊሰር ጽህፈት ቤቱ ለስልጠና ለእርሱ ያወጣውን ማናቸውም ወጪ መክፈል ይኖርበታል፡፡

፲፩. **<u>የቁጥጥር ኦፊሰሮች ተግባርና ግዴታ</u>**

ማንኛውም የቁጥጥር ኦፊሰር፡-

፩. በዚህ ደንብና በሌሎች የደንብ መተላለፍን በሚመለከት በስራ ላይ ባሉ ደንቦች መሠረት የመከላከል፣ የመቆጣጠርና እርምጃ የመውሰድ ተግባር ያከናውናል፣

፪. ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሥራ መለያ ልብስ መልበስና ማንነቱን የሚገልጽ የደረት ባጅ በማንጠልጠል በግልጽ እንዲታይ ማድረግ አለበት፣

፫. በተመደበበት የስራ ክልል በማንኛውም ጊዜ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን ያከናወናል፣

፬. ሕገወጥ ግንባታ መፈፀሙን ሲመለከት ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ወደ ማንኛውም ግቢ በመግባት በዚህ ደንብ መሠረት ሕገወጥ ግንባታውን የመከላከል፣ የመቆጣጠርና ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፣ ሆኖም ከህግ አግባብ ውጪ በሰው መብትና ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፣

፭. በዚህ ደንብ መሠረት የደንብ ጥሰት ለፈፀመ ማንኛውም ሰው ተገቢውን የቅጣት ማስታወቂያ ፎርም በመሙላት ይሰጣል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት መቀጮውን ገቢ ያላደረገ ደንብ ተላላፊ በደንቡ መሠረት ገቢ ያላደረገውን መቀጮ ተፈጻሚ እንዲሆን ለወረዳው የሥራ ሂደት ያሳውቃል፣

፯. ማንኛውም ሰው የፈፀመው የደንብ ጥሰት በዚህ ደንብ ከተመለከተው በተጨማሪ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ከሆነ ተቆጣጣሪ ኦፊሰሩ ከተገቢው ማስረጃ ጋር ጉዳዩን ለሚመለተው አካል ማቅረብ አለበት፣

8. A control officer who resigns before the compulsory service period specified under sub-article 7 of this Article shall reimburse to the Office any expense incurred on him for training.

11. **<u>Function and Duty of the Control Officers</u>**

A control officer shall:

1. Perform the function of preventing, controling and taking measures on code violations covered by this Regulation and others related laws;
2. Dress uniform and put on a tag which clearly shows his identity when he perform his job ;
3. Perform the task of prevention and control at any time within the assigned boundary;
4. Prevent, control and take the necessary measure by entering in to any premise whenever he encounters illegal construction or he receives information; however, he shall be accountable to any damage caused against the right and property of persons by acting contrary to the law;
5. Fill in and issue the appropriate penalty notice form to any code violator persuant to this Regulation; and shall followup its execution;
6. Inform the Wereda business process about the violator who has not paid the penalty in accordance with Sub-Article 5 of this Article to discharege the fine;
7. Present to the appropriate organ with the relevant evidence in case where the committed illicit act is punishable by criminal law in addition to those covered by this Regulation;

፰.በከተማው አስተዳዳር የመንግስት ሰራተኛ አስተዳደር ሕግ የተመለከተው የስነምግባር መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ በጽህፈት ቤቱ የሚወጣውን የሥነ-ምግባር መመሪያ በመከተል ስራውን ሊፈጽም ይገባል፤

፱. በወረዳው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የሚሰጡትን የሥራ ግዴታዎች በአግባቡ የመወጣት ኃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## ስለተከለከሉ ድርጊቶች

**፲፪. ስለ ሕገወጥ የመሬት ወረራ እና ሕገወጥ ግንባታ ስለመከልከሉ**

በሌሎች ህጐች መሠረት የሚከተሉት የተከለከሉ ናቸው፡-

፩. የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅና ደንብ በመተላለፍ ህገ ወጥ የመሬት ወረራና ማስፋፋት እና ሕገወጥ ግንባታ ማካሄድ፤

፪. ስለ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ የወጣውን ደንብ በመተላለፍ ደረቅ ወይም ፈሳሽ ቆሻሻ በከተማው ክልል ባልተፈቀደ ቦታ መጣል ወይም መልቀቅ፤

፫. ስለ መንገድ አጠባበቅ በወጣው ደንብ መሠረት የመንገድን ደህንነት የሚጐዱ ተግባራትን መፈፀም ፤

፬. ስለ ውጭ ማስታወቂያ የወጣውን ደንብ በመተላለፍ የከተማውን ጽዳትና ውበት የሚያበላሽ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ መትከል፣ መገንባት፣ ማንጠልጠል፣ ማሠራጨት፡፡

8. Notwithstanding those ethical principles stipulated on the City Governments Civil Servant law, he shall perform his activities in accordance with a code of ethics issued by the Office;
9. Discharge other obligations which may be entrusted to him by the Woreda Code Enforcement Office.

## PART FOUR
## PROHIBITED ACTS

**12. Prohibition of Illegal Invasion of Land and Illegal Construction**

The following are prohibited in accordance with other laws:

1. Illegal possession and expansion of land, and illegal building in violation of the Urban Land Lease Proclamation and Regulation;
2. Disposal of solid or liquid waste in a place not allwed within the boundary of the City in violation of the Regulation providing for the management, collection and disposal of waste;
3. Performing any activity endangering the safety of roads in violation of the Regulation provide for preservation of roads;
4. Affixing, erecting, building, hanging, distributing outdoor advertisement that affects hygiene and beauty of the City in violation of the Regulation which provide for outdoor advertisement.

፲፫. **ጫት ማስቃም ፣ ሺሻ ማስጨስ እና የጎዳና ንግድ ስለመከልከሉ**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የተከለከሉ ድርጊቶች ናቸው፡-

፩. ጫት ማስቃም ወይም ሺሻ ማስጨስ፣

፪. በማንኛውም ትምህርት ተቋም ዙሪያ፡-

ሀ. ፊልም ወይም ቪዲዮ ማሳየት፣

ለ. የቀንም ሆነ የሌሊት የጭፈራ ቤት ንግድ ሥራ ማከናወን፣

ሐ. ማንኛውንም ዓይነት የአልኮል መጠጥ መሸጥ፣

መ. ቁማር መጫወት ወይም ማጫወት፣

፫. በሚመለከተው የከተማ አስተዳደር አካል ካልተፈቀደ በስተቀር የጎዳና ንግድ ማከና ወን፡፡

**ክፍል አምስት**

**ስለሕገወጥ ንብረት አወራረስ፣ አሻሻጥና አወጋገድ**

፲፬. **ንብረት ስለመውረስ**

፩. ይህን ደንብ በመተላለፍ በመንገድ ላይ ሕገወጥ ንግድ ሲካሄድበት የተገኘ ሸቀጥ ወይም ንብረት ይወረሳል፣

፪. በመንገድ ላይ ለንግድ ወይም ለሌላ ማንኛ ውም ተግባር የተቀመጠ ዕቃ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ካልተነሳ ይወረሳል፣

፫. ይህን ደንብ በመተላለፍ የተከናወነ ሕገወጥ ግንባታ በሚኖርበት ወቅት ግንባታውን ያከና ወነው ሰው በ፫ ቀናት ጊዜ ውስጥ ግንባታውን እንዲያፈርስ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደ ርሰው ይደረጋል፣

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ሕገወጥ ግንባታውን እንዲያፈርስ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በተጠቀሰው ጊዜ ግንባታውን ለማፍረስ ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ግንባታውን በማፍረስ ንብረቱ ይወረሳል፣

13. **Prohibition of Causing the Chewing Chat, Smoking of Shisha and Street Vendering**

The following acts shall be prohibited:

1. To cause chewing chat and smoking of shisha;
2. Around any education institution:
   a. Showing film or video;
   b. Carrying out day time or night time dance club activities;
   c. Selling any kind of alcoholic beverage;
   d. Gambling or cause gambling;
3. Street vendering except permitted by the relevant organ of the City Government.

**PART FIVE**

**CONFISCATIION SALE AND DISPOSAL OF ILLEGAL PROPERTY**

14. **Confiscating Property**

1. An item or property which is the subject of illegal street vendering in violation of this Regulation shall be confiscated;
2. A property deposited on road for commercial or any other purpose shall be confiscated, if it is not removed based on the notice thereof;
3. Whenever there is illegal construction under taken by violating this Regulation written notice shall be given to the person to demolish within three days;
4. If the illegal constructor is unwilling to demolish the construction in accordance with the notice issued under sub-article 3 of this Article, the construction shall be demolished and the property shall be confiscated;

፭. ሕገወጥ ግንባታውን ለማፍረስ የወጣውን ወጪ ህገ ወጥ ገንቢው መተካት አለበት፡፡

**፲፭. <u>ስለተወረሰ ንብረት አያያዝ</u>**

፩. ተቆጣጣሪ ኦፊሰሮች ይህ ደንብ በመጣሱ የተወረሰን ንብረት በየወረዳው ለሚገኘው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ያስረክባሉ፤

፪. የተወረሰውን ንብረት ወደ ወረዳው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ለማድረስ የወጣውን ወጪ ንብረቱ የተወረሰበት ሰው የመሸፈን ግዴታ አለበት፤

፫. የወረዳው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የተወረሰን ንብረት በአግባቡ በመጠበቅ ይይዛል፤ መያዙን ያረጋግጣል፤

፬. የወረዳው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የተወረሰ ንብረትን እንደ ንብረቱ ልዩ ባህሪ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

**፲፮. <u>ስለተወረሰ ንብረት አሻሻጥ እና አወጋገድ</u>**

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የተወረሰ ንብረት በግልጽ ጨረታ ይሸጣል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በጨረታ ሊሸጥ የማይችል ማንኛውም የተወረሰ ንብረት በከተማ አስተዳደሩ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሠረት በመሰረዝ ይወገዳል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ከጨረታ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ በከተማው አስተዳደር ፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ለወረዳው ፋይናንስ ጽህፈት ቤት ገቢ መደረግ አለበት፤

፬. በዚህ አንቀጽ ስለተወረሰ ንብረት አሻሻጥ እና አወጋገድ ዝርዝር አፈፃፀምን በተመለከተ ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

5. The cost of demolishing the illegal construction shall be covered by the illegal constructor.

**15. <u>Keeping of Confiscated Property</u>**

1. Control officers shall deliver the property confiscated due to violating this Regulation to the respective Wereda Code Enforcement Office;
2. The cost incurred to move or transport the property to the Wereda Code Enforcement Office shall be covered by the person whose property is confiscated;
3. The Wereda Code Enforcement Office shall properly keep the confiscated property; ensure its proper keeping ;
4. The Wereda Code Enforcement Office shall cause the storage of confiscated property by considering its peculiar feature.

**16. <u>Selling and Disposal of Confiscated Property</u>**

1. A property confiscated in accordance with this Regulation shall sell by open tender;
2. Confiscated property which can't be sell in accordance with sub-article 1 of this Article, shall be disposed by delition based on the City Government's procurement and property administration law;
3. The revenue generated from the tender sale in accordance with sub-article 1 of this Article shall be deposited to the Wereda Finance Office based on the City Governments financial administration law;
4. Particulars about selling and disposing of confiscated property stated by this Article shall be determined by directive to be issued by the Office.

## ክፍል ስድስት
## ስለቅጣትና አቤቱታ አቀራረብ

### ፲፯. ስለቅጣትና እርምጃ

፩. በወንጀል ሕግ እና በሌላ ሕግ የተመለከተው ኃላፊነትና ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ደንብ የጣሰ ማንኛውንም ሰው፡-

ሀ. እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ፣ የማስነሳት እርምጃ የቁጥጥር ኦፊሰሮች ይወስዱበታል፤ እንዲሁም

ለ. ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፤

፪. በዚህ ደንብ መሠረት ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ደንብ የተላለፈ ሰው በተቆጣጣሪ ኦፊሰር የተሰጠውን የቅጣት ማስታወቂያ በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ በሚገኘው የሥራ ሂደት መቀጮ ገቢ ማድረግ አለበት፤

፫. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የቅጣት ማስታወቂያ ፎርም ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ ተቆጣጣሪ ኦፊሰሩ ከአካባቢው ፖሊስ ጋር በመተባበር የቅጣት ማስታወቂያውን እንዲቀበል ያስገድዳል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት መቀጮውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት መቀጮ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት መቀጮውን ገቢ ለማድረግ ያልቻለ ወይም ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው በማህበራዊ ፍርድ ቤት እስከ ሶስት ወር በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ሊቀጣ ይችላል፡፡

## PART SIX
## PENALTY AND COMPLAINT LODGING

### 17. Penalty and Measure

1. Without prejudice to the penalties imposed by the Criminal Code and other laws, any person who violated this Regulation :
   a. according to the nature of the violation the control officer shall take the measure of stopping the activity, closing, sealing, removing; and
   b. punishable with administrative penalties in accordance with the annexed schedule of this Regulation.
2. Any person who has been penalized in accordance with this Regulation shall pay the fine by annexing the notice given to him by the control officer to the Wereda business process situated in the area where the violation was commited;
3. If the offender is unwilling to take the penalty notice in accordance with sub-article 2 of this Article, the control officer in collaboration with the police shall force him to receive the same;
4. Any person who is unwilling to deposite the fine in accordance with sub-article 2 of this Article shall be made to pay double of the imposed penalty;
5. Any person who is unable or unwilling to pay the fine in accordance with sub-article 4 of this Article may be punishable with arrest up to three month by social court.

**፲፰. <u>ስለተደጋጋሚ ጥፋትና ቅጣት</u>**

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፯ የተደነገገው ቢኖርም በተደጋጋሚ የደንብ መተላለፍ የፈፀመ ማንኛውም ሰው የሚቀጣው ቅጣት እጥፍ ይሆናል፡፡

**፲፱. <u>ቅጣትን ስለማስፈፀም</u>**

፩. በክፍለ ከተማ ፍትህ ጽህፈት ቤት ስር የሚመለከተው የስራ ሂደት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው መሠረት መቀጮውን ገቢ ያላደረገን ሰው ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ በሚገኘው ማህበራዊ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ቅጣቱን ያስፈጽማል፤

፪. ማህበራዊ ፍርድ ቤት በዚህ ደንብ የተመለከተውን የደንብ መተላለፍ መቀጮ በቀረበለት መሠረት ያስፈጽማል፡፡

**፳.<u>ስለአቤቱታ አቀራረብ</u>**

፩ ይህንን ደንብ በመተላለፍ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የቅጣቱ ማስታወቂያ ከተሰጠው ቀን አንስቶ በ፫ የስራ ቀናት ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ ለሚገኘው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ሊያቀርብ ይችላል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው ተቀጭው መቀጮ የከፈለበትን ደረሰኝ አያይዞ ሲያቀርብ ነው፤

፫. የወረዳው ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የቀረበውን አቤቱታ ከዚህ ደንብና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር በቀረበው አቤቱታ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

፬. አቤቱታው ተመርምሮ የተከፈለው ቅጣት አላግባብ መሆኑ ሲረጋገጥ በከተማው አስተዳደር ፋይናንስ ሥርዓት መሠረት ቅጣት የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ይሆናል፡፡

**18. <u>Recidivism</u>**

Notwithstanding the provision of Article 17 of this Regulation, the penality imposed on a person who repeatedly commits code violations shall be double.

**19. <u>Execution of Penalty</u>**

1. When a person failed to pay the fine in accordance with sub-article 2 of Article 17, the relevant business process of the Sub-City Justice Office shall cause the implementation of the penalty by presenting the case before a Social Court situated in place where the violation was commited;
2. The Social Court shall execute the fine for code violations covered by this Regulation as per the presentment;

**20. <u>Complaint Lodging</u>**

1. Any person, who has been imposed penalty up on by violating this Regulation, shall lodge his compliant to the respective Wereda Code Enforcement Office within 3 working days from the date issued;
2. In accordance with sub-article 1 of this Article to lodge complain the penalized person shall annex the payment receipt of the penalty;
3. The Wereda Code Enforcement Office shall give decision on the case submitted to it by taking into consideration this Regulation and other relevant laws;
4. Where it is proved upon investigation that the penalty was imposed improperly, the money so paid shall be refunded in accordance with the financial procedures of the City Government.

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፩. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፳፪. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ጽህፈት ቤቱ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ፳፫. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፩. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ አጠበባበቅ ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፺፭ አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ "ሀ" በትራፊክ ፖሊስ እንዲፈፀሙ ከተመለከቱት ጥፋቶች በስተቀር ሌሎች በደንቡ የተዘረዘሩት የጥፋት አይነቶች በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቆሻሻ አያያዝ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፮ አባሪ የሆነው የቅጣት ጠንጠረዥ ተሽሮ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ተተክቷል፡፡

፫. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### ፳፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፭ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**ጥቅምት ፳፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## PART SEVEN

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 21. Duty to Cooperate

Any person shall have the duty to obey and enforce this Regulation.

### 22. Power to Issue Directives

The Office may issue directives for the implementation of this Regulation.

### 23. Repealed and Inapplicable laws

1. Except those offences stipulated to be enforced by the traffic police under the Addis Ababa City Government Preservation of Roads Regulation No. 2/2003 schedule "A", other listed offences are repealed by this Regulation.
2. The annexed penalty schedule of the Addis Ababa City Waste Management Collection and Disposal Regulation No. 13/2004 is repealed by this Regulation.
3. Any Regulation, directive or customary practice which is inconsistent with matters covered by this Regulation shall have no effect.

### 24. Effective Date

This Regulation shall enter into force as of the 8th day of July 2013.

**Addis Ababa**
**1st Day of December, 2012**

**Kuma Demeksa**
**Mayor of Addis Ababa City**

## የቅጣት ሰንጠረዥ ፩

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | አግባብ ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ ሳያገኝ የመንግ ስትን መሬት በማናቸውም መንገድ መያዝ | ብር ፭ሺ |
| ፪ | በህጋዊ መንገድ ከተያዘው የቦታ ስፋት መጠን በላይ የመንግሰት መሬት አስፋፍቶ መያዝ | ብር ፫ሺ |
| ፫ | አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ የመንግስትን መሬት በመያዝ ወይም ህጋዊ ይዞታን በማስፋፋት ህገወጥ ግንባታ መገንባት | ብር ፯ሺ፭መቶ |
| ፬ | በሕጋዊ የመሬት ይዞታ ላይ አግባብ ካለው አካል የግንባታ ፈቃድ ሳያገኝ ማንኛውም ግንባታ ማካሄድ | ብር ፪ሺ |

## የቅጣት ሰንጠረዥ ፪

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | ቆሻሻ በአግባቡ አለመያዝ ወይም ማዝረክረክ<br>• ከመኖሪያ ቤት ከሆነ<br>• ከድርጅት ከሆነ | <br>ብር ፩ መቶ<br>ብር ፪ መቶ |
| ፪ | የመኖሪያ ቤትን ወይም የድር ጅትን ፊት ለፊት ያለውን የአካባቢ ንጽህና በአግባቡ አለመጠበቅ<br>• ከመኖሪያ ቤት ከሆነ<br>• ከድርጅት ከሆነ | <br>ብር ፶<br>ብር ፻ |

## Penalty Schedule 1

| No | Types of Violations | Amount of fine |
|---|---|---|
| 1 | Possessing Government land without securing permittion from appropriate Government organ | Birr 5000 |
| 2 | Expanding Government land into possession inaddition to legally entitled plot | Birr 3000 |
| 3 | Undertaking illegal construction by possessing Government land withot permission or by expanding legal possession without permission | Birr 7500 |
| 4 | Undertaking any kind of construction on legally possed land without securing permittion from the appropriate Government organ | Birr 2000 |

## Penalty Schedule 2

| No | Types of Violations | Amount of fine |
|---|---|---|
| 1 | Littering or mismanagement of waste<br>• House hold<br>• Organization | <br>Birr 100<br>Birr 200 |
| 2 | Failure to properly Keep front of house hold or organization clean<br>• Form house hold<br>• From organization | <br>Birr 50<br>Birr 100 |

| | | |
|---|---|---|
| ፫ | ደረቅ ቆሻሻ ባልተፈቀደ ቦታ መጣል<br>• ከመኖሪያ ቤት<br>• ከኢንዱስትሪ<br>• ከጤና ተቋም<br>• ከሌሎች ድርጅቶች | <br>ብር ፩ መቶ<br>ብር ፯ሺ<br>ብር ፭ሺ<br>ብር ፩ሺ |
| ፬ | ጥቃቅን ቆሻሻዎችን ተገቢ ባልሆኑ ቦታዎች መወርወር | ብር ፩መቶ |
| ፭ | ባልተፈቀደ ቦታ ላይ አሮጌ መኪና፣ ቆርቆሮ፣ አሸዋ፣ አፈር፣ ወዘተ መቆለልና ማስቀመጥ | ብር ፭መቶ |
| ፮ | ከገንዳ ውጭ ቆሻሻ መድፋት | ብር ፲ |
| ፯ | የጥቃቅን ቆሻሻ መያዣዎችን አለአግባብ መጠቀም ወይም ማበላሸት | ብር ፫መቶ |
| ፰ | ቆሻሻን እያዝረከረኩና ሳይሸፈኑ ማሽከርከር | ብር ፶ |
| ፱ | ከተሽከርካሪዎች ላይ በመሆን ቆሻሻዎችን የሚወረውር አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ | ብር ፩ |
| ፲ | በእንስሳት እርባታና የማቆያ ቦታዎች ቆሻሻዎችን በአግባቡ አለመያዝና አለማስወገድ | ብር ፭ መቶ |
| ፲፩ | የቀንድና የጋማ ከብት እንደዚሁም ውሾችን ወይም ለማዳ እንስሳትን ይዞ በመዞር ባልተፈቀደ ቦታ እንስሳቱን ማፀዳዳት | ብር ፪ መቶ |
| ፲፪ | ያልተሸፈነ ጭነት በጋማ ከብት በማጓጓዝ ከተማ ማቆሸሽ | ብር ፫ መቶ |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | Dumping solid waste in an unauthorized place<br>• From house hold<br>• From industry<br>• From health institution<br>• From other organization | <br>Birr 100<br>Birr 7000<br>Birr 5000<br>Birr 1000 |
| 4 | Throwing sweepings to inpropriate places | Birr 100 |
| 5 | Dump old car, corrugated sheet of iron, sand, soil etc or pie them up. | Birr 500 |
| 6 | Dump waste outside the dumpsteres | Birr 10 |
| 7 | Failure to handle properly sweeping containers | Birr 300 |
| 8 | Failure to cover waste and littering it while driving on vehicles | Birr 50 |
| 9 | A passenger or deriver throwing waste out of the car | Birr 100 |
| 10 | Failure to handle and dispose duly waste, generated from animal rearing or bare places | Birr 500 |
| 11 | Keeping animals like cattle, equine and dog with on self and allow them to defecate or urinate in an unauthorized place | Birr 200 |
| 12 | Teansproting the uncover load on equines and thereby make the city dirty | Birr 300 |

| | | |
|---|---|---|
| ፲፫ | የሞቱ እንስሳት ባልተፈቀደ ቦታ ሲጥል የተገኘና የተረጋገጠበት<br>• የቀንድ ከብት<br>• ሌሎች እንስሳት | ብር ፫መቶ<br>ብር ፪መቶ |
| ፲፬ | ህገ ወጥ እርድ<br>• አራጅ<br>• ተጠቃሚ ግለሰብ<br>• ተጠቃሚ ድርጅት | ብር ፭ ሺ<br>ብር፩ ሺ፭መቶ<br>ብር፯ ሺ፭መቶ |
| ፲፭ | የቀንድ ከብትና የመሳሰሉትን ባልተፈቀዱ ቦታዎች ላይ በማቆየት ከተማ ማቆሸሽ | ብር ፪መቶ |
| ፲፮ | ከግንባታ ወይም ከፍርስራሽ የሚመነጭ ቆሻሻ ወይም አፈር ባልተፈቀደ ቦታ መጣል | ብር ፭መቶ |
| ፲፯ | ልዩ ቆሻሻዎችን በአግባቡ አለመያዝ ወይም አለመጣል | ብር ፭መቶ |
| ፲፰ | አደገኛ ቆሻሻዎችን በአግባቡ አለመያዝና አለማስወገድ<br>• የኢንዱስትሪ ከሆነ<br>• የጤና ተቋም ከሆነ | ብር ፩ ሺ<br>ብር ፯ ሺ |
| ፲፱ | ባልተፈቀደ ቦታና ሁኔታ ቆሻሻ፣ ሬንጅ፣ ፕላስቲክ ወይም የመሳሰሉትን ማቃጠል<br>• ግለሰብ<br>• ድርጅት | ብር ፪ መቶ<br>ብር ፭ መቶ |
| ፳ | የገበያ ቦታ አቆሸሾ መነሣት | ብር ፫ መቶ |
| ፳፩ | በአገልግሎት ተቋማትና የማምረቻ ድርጅቶች ተገቢ የሆነ የጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ<br>• አለማስቀመጥ<br>• በአግባቡ አለማስወገድ | ብር ፪ መቶ<br>ብር ፩ መቶ |
| ፳፪ | በመንገድ ወይም ከመፀዳጃ ቤት ውጭ ሽንት መሽናት ወይም መጸዳዳት | ብር ፶ |

| | | |
|---|---|---|
| 13 | The one who is found and proven dumping dead animals in an unauthorized place<br>• Cattle<br>• Other domestic animals | Birr 300<br>Birr 200 |
| 14 | Illegal slaughtering<br>• Slaughter<br>• Benefciary person<br>• Beneficiary organization | Birr 5000<br>Birr 1500<br>Birr 7500 |
| 15 | Allowing cattle to stay in an unatuthorized places and make the city dirty | Birr 200 |
| 16 | To dump, waste and earth generated from constriction and demolition in an unatuhoirzed places | Birr 500 |
| 17 | Not duly handle or dispose especial waste | Birr 500 |
| 18 | Not duly handle or dispose hazardous waste<br>• For industry<br>• For health institution | Birr 1000<br>Birr 7000 |
| 19 | Burn waste bitumen plastic or other similar material in an unauthorized place and condition<br>• Individual person<br>• Organization | Birr 200<br>Birr 500 |
| 20 | To leave the market place, unclean after use | Birr 300 |
| 21 | Failure to place sweeping containers in service rendering or manufacturing organizations<br>• Not Placing<br>• Improper disposal | Birr 200<br>Birr 100 |
| 22 | Deficating on the road or outside toilet | Birr 50 |

## የቅጣት ሰንጠረዥ ፫

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | ለግንባታም ሆነ ለሌላ ጉዳይ የሚሆኑ ድንጋይ፣ አሸዋ፣ አፈር፣ ወዘተ መንገድ ላይ ማራገፍ | ብር ፩ ሺ |
| ፪ | ለግንባታም ሆነ ለሌላ ጉዳይ የሚሆኑ ድንጋይ በመንገድ ላይ መፍለጥ ወይም መጥረብ | ብር፭ መቶ |
| ፫ | በመንገድ ላይ ጭቃ ማቡካትም ሆነ ማንኛውም መሰናክል ማድረግ | ብር፭ መቶ |
| ፬ | የንግድ ዕቃ ወይም ሌላ ዕቃ ለአጭርም ሆነ ለረጅም ጊዜ ማስቀመጥ | ብር ፫ መቶ |
| ፭ | ማንኛውም ሰው በሕጋዊ መንገድ ከያዘው ይዞታ ውጭ በመሆን መንገድን፣ በማስተር ኘላኑ መሠረት ለመንገድነት የተያዙ ክፍት ቦታዎችን፣በመንገዶች ግራና ቀኝ ያሉ የእግረኛ መንገድን የሸቀጥ እቃዎችን ደርድሮ በማስቀመጥ ወይም ለጠጠ ቃሚ የሚሆን ወንበሮችን መደር ደር፣ ዛፍና አትክልት በመትከል መንገደ ኛንም ሆነ ተሽከርካሪን ማሰናከል፣ መንገድ ላይ “ማቆም ክልክል ነው” የሚል ወይም መሰል ምልክቶችም ሆነ ማናቸውንም ግንባታ ማቆም፣ ቤት መሥራትና አጥር ማጠር፣ | ብር ፫ሺ |
| ፮ | በመንገድ ላይ ከብት ማሰማራት የከብት ንግድ ማካሄድ | ብር ፷ |
| ፯ | አውቆም ሆነ በድንገተኛ ሁኔታ በድል ድዮች፣ በመንገድ መብራቶችና ቋሚ ዎች (ፖሎች)፣ በትራፊክ ምልክ ቶች፣ በትራፊክ መብራቶች በእግረኛ መከላ ከያዎች፣ በማንሆሎች፣ በፍካዎች ወይም በክዳኖቻቸው ላይ ጉዳት ማድረስ | ብር፭ መቶ |

## Penalty Schedule 3

| No | Types of Violations | Amount of fine |
|---|---|---|
| 1 | Dump stones, sand, soil and the like on the road for the purpose of construction or otherwise | Birr 1000 |
| 2 | Break or chisel stones for the purpose of construction or otherwise on the road | Birr 500 |
| 3 | Mix soil; put permanent or temporary barricade or obstruction on the road. | Birr 500 |
| 4 | Put commercial or other items neither for longer period nor for the time being on the road | Birr 300 |
| 5 | Outside their possession recogniazed by law, put up items for sale, set up chairs for use in open air, plant trees and plant on roads, on open spaces reseved for roads as per the Master plan, on both sides of pedestrian roads, put up signs like “No Parking” or similar signs or objects that serve the same including construct houses and fence | Birr 3000 |
| 6 | Deploying, trading cattle on the road | Birr 60 |
| 7 | Causing damages, intentionally or accidentally, to properties and bridges, road side lights and their poles, traffic signs, traffic lights, pedestrian burriers, manholes, manhole covers, median barriers | Birr 500 |

| | | |
|---|---|---|
| ፰ | መንገዶችን ማሻሻል፣ መቀየር ፣ መቀየስ፣ በበር መዝጋት፣ በኬላ ማጠር፣ መቁረጥ፣ መስበር፣ መቆፈር ወይም በሌላ ሁኔታ ተሽከርካሪም ሆነ እግረኛ እንዳይተላለፍ ማድረግ | ብር ፩ ሺ |
| ፱ | የዋና መንገዶች በማናቸውም ምክንያቶች አለመዘጋት እንደተጠበቀ ሆኖ በኀዘን ምክንያት ሳይሆን የእግረኛንም ሆነ የተሽከርካሪን መንገድ ድንኳን በመጣል(በመትከል) በከፊልም ሆነ በሙሉ መዝጋት | ብር፩ መቶ ፵ |
| ፲ | በመንገድ ላይ የግንባታ ተረፈ ውጤቶችን መድፋት | ብር ፩ ሺ |
| ፲፩ | ሆን ብሎ የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽ ከመንገድ ጋር ማገናኘት እና መልቀቅ | ብር ፩ ሺ |
| ፲፪ | መንገድ ላይ የተበላሸ ተሽከርካሪ መጠገን; ድንጋይ መደርደር፣ የተጫነን ማንኛውም ነገር ማንጠባጠብ ወይም መጣል | ብር ፩ ሺ |
| ፲፫ | በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ ማሳጠብ | ብር ፪ መቶ |
| ፲፬ | በተወሰኑ ቀናት የንግድ ስራን ለመነገድ ተለይተው ከተፈቀዱበት መንገዶች በስተቀር የንግድ ሥራን በመንገድ ላይ ማካሄድ | ብር ፭ መቶ |
| ፲፭ | በመንገዶች፣ በድልድዮች በትራፊክ መብራቶች፣ ምልክቶች፣በፖሎች ወይም በእግረኛ መከላከያ ያለፈቃድ ማስታወቂያ ወይም ባነር መለጠፍ ወይም ማንጠልጠል | ብር ፭ መቶ |

| | | |
|---|---|---|
| 8 | Upgrade, change, survey, close, barricade roads; cut, break, dig; or in any other way prevent passage of either pedestrians or vehicles. | Birr 1000 |
| 9 | With the reservation that main roads are not to be blocked for any reason, blockage of roads or pedestrians totally or partially with tent for a reason other than mourning | Birr 140 |
| 10 | Dump construction wastes, soil, and others on the road | Birr 1000 |
| 11 | Intentionally connecting sewerage or septic tank with roads | Birr 1000 |
| 12 | Repair vehicles; put stones on the road, drip or drop items and things that one is transporting | Birr 1000 |
| 13 | Cause vehicle to be washed on roads | Birr 200 |
| 14 | Undertaking street vendering except on those roads specifically permitted to do so for limited days | Birr 500 |
| 15 | Fixing or tagging advertisement or banners without permission on roads, bridges, traffic lights, signs, poles or pedestrian barriers | Birr 500 |

## የቅጣት ሰንጠረዥ 4

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | ጫት ማስቃም | ብር ፩ ሺ.፭ መቶ |
| ፪ | ሺሻ ማስጨስ | ብር ፩ ሺ. |
| ፫ | በትምህርት ተቋማት ዙሪያ፡- | |
| | • ፊልም ወይም ቪዲዮ ማሳየት | ብር ፩ ሺ. |
| | • የቀንም ሆነ የሌሊት የጭፈራ የንግድ ሥራ ማከናወን | ብር ፪ ሺ. |
| | • ማንኛውንም ዓይነት የአልኮልን መጠጥ መሸጥ | ብር ፫ ሺ. |
| | • ቁማር መጫወት ወይም ማጫወት | ብር ፩ ሺ. |

## Penalty Schedule 4

| No | Types of Violations | Amount of fine |
|---|---|---|
| 1 | Cause the chewing of chat | Birr 1500 |
| 2 | Cause the smoking of shisha | Birr 1000 |
| 3 | Around any educational institution: | |
| | • Showing film or video | Birr 1000 |
| | • Carrying out dance club business at night or day time | Birr 2000 |
| | • Selling any kind of alcoholic beaverages | Birr 3000 |
| | • Gambling or cause gambling | Birr 1000 |